# ምዕራፍ ስምንት

## መገናኛ ብዙሃን

**የምዕራፉ ዓላማዎች:- ተማሪዎች! ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፣**

- የመገናኛ ብዙሃን አገልግሎትና ጠቀሜታን ትገልጻላችሁ፡፡
- በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን የሚተላለፉ መልእክቶችን አዳምጣችሁ ትገልጻላችሁ፡፡
- በመሸጋገርያና አያያዥ ቃላት ተጠቅማችሁ ሐረጎችንና ዓረፍተነገሮችን ትመሰርታላችሁ፡፡
- የአንቀፅ አጻጻፍ ሥርዓትን ተከትላችሁ ተገቢዎችን መሸጋገርያ ቃላት በመጠቀም አንቀጽ ትጽፋላችሁ፡፡
- ከአካባቢያችሁና ከመገናኛ ብዙሃን የደስታ፣ የኀዘንና የሥራ ግጥሞችን ትሰበስባላችሁ፡፡
- ሥርዓት ጠብቃችሁ ትወያያላችሁ፤ ትጨዋወታላችሁ፡፡
- የሥራ ደብዳቤ ትጽፋላችሁ፡፡
- ከተለያዩ ጭውውቶችና ገለጻዎች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በማስታወሻ ትይዛላችሁ፡፡

© MoE, FD[...] Not to be rep[...]d

© MoE, FDRE Not to be republished

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

፩. መገናኛ ብዙሃን ተብለው የሚጠቀሱት የትኞቹ ናቸው? ዘርዝሩ።
፪. አዘውትራችሁ የምትከታተሉት የትኛውን መገናኛ ብዙሃን ነው? ለምን?
፫. መገናኛ ብዙሃን ባይኖሩ ምን የሚከሰት ይመስላችኋል?
፬. ከተለያዩ መገናኛ ብዙሃን መረጃ ለማግኘት የሚፈልግ ሰው ምን ማድረግ አለበት ትላላችሁ?
፭. ርዕሱንና የመጀመሪያውን አንቀፅ አንብቡና ምንባቡ ስለምን ሊያወሳ እንደሚችል ጥንድ ሆናችሁ በመወያየት ገምቱ።

## "ለወሬ ሞትኩ ደበሉ"

ጧት ጧት ከመኝታዬ ተነስቼ ፊቴንና እጆቼን ታጥቤ ወደ ሳሎን እንደገባሁ ሬዲዮኤን ከፍቼ ዜና መስማት የቆየ ልማዴ ሆኗል። የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥንን፣ እንዲሁም ሌሎች የሀገራችን ሬዲዮ ጣቢያዎችን፣ “ቢ.ቢ.ሲ.”ንም ሆነ “ቮይስ ኦፍ አሜሪካ”ን “ዶቸቬሌ”ንም ሆነ “ሬዲዮ ፍራንስ ኢንተርናሽናል”ን ወይም ሌላ ሬዲዮ ጣቢያ ስከፍት፣

"አሜሪካን አገር ውስጥ በከፍተኛ ፍጥነት የሚገሰግስ አውሎ ንፋስ ከባድ ጉዳት አደረሰ..."፤

“ጃፓን ከፍተኛ የሆነ የመሬት መንቀጥቀጥ ደረሰባት፤ የመሬት መንቀጥቀጡ ‘ሱናሚ’ም ያስከተለ ነበር”፤

"ሕንድ አገር ውስጥ የመሬት ነውጥ ተከስቶ ብዙ ሕዝብ አለቀ..."፤

"ቻይና ውስጥ በተወሰነ አካባቢ ርእደ መሬት ደረሰ።"

የሚሉ እና ሌሎችም የተለያዩ ዜናዎች በየጊዜው አገኛለሁ። ለኔም ይሁን እንደኔ ላሉት እንዲህ ዓይነት ዜናዎችና ሌሎችም ምን ይረቡ ይሆን? የሰው ልጅ ሕይወት ተመሳሳይነት ስላለው ይሆን በሌሎች አገሮች የተከሰተውን ዜና ለመስማት ጉጉት የሚያድርብን? “ከዚህ ጋር ግንኙነት ያለው አደጋ ወይም ጉዳት በኔም አገር ሊከሰት ይችላል” በሚል ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ ፍራቻ የዓለምን ዜና የምንከታተል ይመስለኛል።

በተጠቀሰውም ምክንያት ይሁን ወይም በሌላ ተመሳሳይ ምክንያት፣ እኔ ብቻ ሳልሆን የመላው ዓለም ሕዝብ፣ ወሬ ፍለጋ በነጋ በጠባ ሬዲዮ እንደሚጎረጉር፣ ቴሌቪዥን እንደሚከፍት፣ ጋዜጦችንና መጽሔቶችን ገዝቶ እደሚያነብ አውቃለሁ፡፡ የሰው ልጅ የማወቅ ፍላጎት ባይኖረው ሬዲዮና ቴሌቪዥን መች በተፈጠሩ ነበር! ጋዜጠኝነትስ መች በተጀመረ ነበር!

ስለ ሰው ልጅ የማወቅ ፍላጎት ሳነሳ፣ አንዲት ሴት ወይዘሮ ትዝ ይሉኛል፡፡ እኚህ የመሥሪያ ቤት ባልደረባዬ ቀልደኛ ቢጤ ነበሩ፡፡ ሁለታችንም እየተከባበርን የምንጠራራው በአንቱታ ነበር፡፡

ታዲያ! እኚህ ቀልደኛ ሴት ወይዘሮ አልፎ አልፎ ቢሮዬ ድረስ ይመጡና እየሳቁ፣ "ለወሬ ሞትኩ ይበሉ... የምነግርዎት አለኝ" ይሉኛል፡፡

እኔም ፈገግ ብዬ፣ “የሚነግሩኝ ካለዎት እንዲሁ ይንገሩኝ እንጂ፣ እኔስ ‘ለወሬ ሞትኩ’ አልልም እላቸዋለሁ”፡፡ ወሬያችንን እንዲህ በሳቅ ከጀመርን በኋላ፣ አንዳንድ አዳዲስ የሰሙትን ነገር አውግተውኝ፣ እኔም ስለ አጫወቱኝ ነገር አመስግኛቸው እሳቸውም ወደ ቢሮአቸው ይመለሳሉ፡፡

እንደጥንቱ አባባል እንኳ፣ "ለወሬ የለውም ፍሬ" ይባል ነበር፤ ነገር ግን ይህ አባባል በዛሬው ዘመን ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ይልቁንስ በዘመናችን የተለያዩ ወሬዎች መረጃዎች ስለሆኑ፣ “ያለመረጃ፣ያለወሬ መኖር የለም ዛሬ!” ቢባል ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

በኢትዮጵያ በ፲፱፻፷፮ ዓ.ም ዮናታን ዲምብልቢ የተባለው ዜና አቅራቢ፣ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ወሎ ውስጥ በድርቅ ምክንያት እንደ ቅጠል ሲረግፉ የነበሩትን አዛውንቶች፣ ጎልማሶች፣ ወጣቶችና፣ ሕጻናትን ፊልም አንስቶ ተደብቆ የነበረውን የረሃብ ዜና ይፋ ባያወጣው ኖሮ፣ የ፲፱፻፷፮ የኢትዮጵያ አብዮት ይከሰት ነበር ብሎ መገመት አይቻልም፡፡ በእርግጥ ለአብዮቱ መቀጣጠል ሌሎች በርካታ ምክንያቶች ነበሩ፡፡ "ለወሬ የለውም ፍሬ" የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ጊዜ ያለፈበት መሆኑን የሚያስረዳን፣ ይህ የተጠቀሰው ሌሎች እርምጃዎችን ያስከተለ ዜና ነው፡፡

© MoE, FDRE Not to be reproduced

© MoE, FDRE Not to be rep

በየጊዜው ዜናዎችን አዘጋጅተው በመገናኛ ብዙሃን የሚያሰራጩት ጋዜጠኞች ስለሆኑ፣ ጋዜጠኛ እና ዜና የተዛመዱ ናቸው። እንዲያውም ጋዜጠኛ ካለ ዜና አለ፤ ዜና ካለ ጋዜጠኛ አለ ማለት ይቻላል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ጋዜጠኝነት የተጀመረው በአፄ ሚኒልክ ዘመነ መንግሥት እንደሆነ ይነገራል። ከዚያ በፊት በኢትዮጵያ የጋዜጠኝነት ሙያ አይታወቅም ነበር። በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግስት ሙያው ተስፋፍቶ የሬዲዮና የቴሌቪዥን አገልግሎቶች ታከሉበት። በኢትዮጵያ እስከደርግ ዘመን የነበረው ጋዜጠኝነት ሙሉ በሙሉ መንግሥታዊ ነበር ለማለት ይቻላል።

የግል ጋዜጠኝነት በሰፊው ሊታይ የቻለው፣ ከ፲፱፻፹፫ ዓ.ም ወዲህ፣ በተለይም የፕሬስ ነጻነት ከታወጀበት ከ፲፱፻፹፬ ዓ.ም ጀምሮ ነው። ከፕሬስ ነፃነት አዋጅ በኋላ፣ በየዕለቱም ባይሆን በየሳምንቱና በየወሩ አዳዲስ ጋዜጦችና መጽሔቶች ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ። በአንድ ወቅት የግል ጋዜጦችና መጽሔቶች በብዛት ይታተሙ ስለነበር፣ "እንደ አሸን ፈሉ!" ተብሎ ነበር። ብዙዎች በግል ይታተሙ የነበሩ ጋዜጦችና መጽሔቶች ግን ዘላቂነት አልታየባቸውም።

*(ሣህለ ሥላሴ ብርሃነ ማርያም፣ 1992፣102-104 ለማስተማርያነት እንዲያገለግል መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተዘጋጀ)።*

## ክፍል አንድ፦ ንባብ

**፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሑፍ አብራርታችሁ መልሱ።**

1. ሰዎች፣ በዓለም ውስጥ የተለያዩ የሬዲዮ ጣቢያዎችን፣ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን እና የሚታተሙ ጋዜጦችና መጽሔቶችን ከመከታተል እና ከማንበብ ምን ያገኛሉ?
2. “ለወሬ ሞትኩ ይበሉ” የሚለው አባባል ምን ማለት ነው?
3. "ለወሬ ሞትኩ ይበሉ" እና "ለወሬ ሞትኩ ለሥራ ሰነፍኩ" ሁለቱ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ይለያያሉ? እንዴት?

© MoE, FDRE Not to be reproduced

4. በቀረበው ጽሑፍ ውስጥ እንግሊዛዊው ጋዜጠኛ ዮናታን ዲምብልቢ እንዴት ሊጠቀስ ቻለ?
5. ዜና እና ጋዜጠኝነት ወይም ጋዜጠኝነትና ዜና ምን ግንኙነት እንዳላቸው ግለጹ፡፡
6. በኢትዮጵያ የጋዜጠኝነት ሙያ የተጀመረው በማን ዘመነ መንግሥት ነው?
7. የግል ጋዜጠኝነት ከመንግሥት ጋዜጠኝነት በምን ይለያል?
8. በኢትዮጵያ የግል ጋዜጠኝነት መቼ ተጀመረ?
9. በኢትዮጵያ፣ የግል ጋዜጠኝነት እንዲጀመር ምክንያት የሆነው ምን ይመስላችኋል?

**፪. ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጎች በምንባቡ ውስጥ የያዙትን ፍች የሚያሳዩ ዓረፍተነገሮች መስርቱና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ፡፡**

ሀ) ዓለም አቀፍ
ለ) ሬዲዮ መኀርኀር
ሐ) "አንቱታ"
መ) ማውጋት
ሠ) እንደቅጠል ሲረግፍ
ረ) ይፋ ማውጣት
ሰ) መቀጣጠል
ሸ) እንደአሸን ፈሉ

## ክፍል ሁለት፡- ጽሕፈት

**፩. በሚቀጥለው ታሪክ ውስጥ ቃልን ከቃል፣ ዓረፍተነገርን ከዓረፍተነገር፣አንቀጽን ከአንቀጽ ያያያዙ መሸጋገሪያና አያያዥ ቃላትን ጥንድ ሆናችሁ ለዩ፡፡**

“በአሥራ ስምንተኛው ምዕተ-ዓመት አጋማሽ ገደማ፣ የሱዳን ጦር ምዕራባዊውን የኢትዮጵያን ድንበር እያለፈ ዘረፋ በማካሄድ የአካባቢውን ሕዝብ በጣም ያስቸግር ነበር፡፡ ከዚህም የተነሣ፣ የወገን ጦር (የኢትዮጵያ ጦር) ከጎንደር በመንቀሳቀስ፣ በሀገሩ ላይ የተቃጣውን ሕገ ወጥ ድርጊት

ለመበቀል ወደ ሰነዓር (በነጭና በጥቁር ዓባይ መካከል በሚገኘው ቦታ) ዘምቶ ተዋግቷል፡፡ በዚህ ወቅት፣ የሀገራቸውን ክብርና የወገናቸውን ደህንነት ለማስከበር ከዘመቱት ሰዎች ጋር ፈረሶችም ይገኙባቸዋል፡፡ ከጌቶቻቸው ጋር ከዘመቱት ፈረሶች መካከልም ሱቤ ወይም ዞብል በመባል ይታወቅ የነበረው ፈረስ ይገኝበታል፡፡ ሱቤ ወይም ዞብል በዚህ ዘመቻ ከጌታው ጋር እንዳለ በጠላት እጅ ወደቀ ወይም ተማረከ፡፡ ሱቤ ወይም ዞብል ከጌታው ጋር ሲማረክ ቆስሎ ወይም ማምለጥ ተስኖትም አልነበረም፤ ነገር ግን ጌታው ሲማረክ ጌታውን ጥሎ ለመሄድ አልፈለገም፡፡"

"ታዲያ የሱዳን ወታደሮች ሱቤ (ዞብል)ን ሲያዩ በግዝፈቱ፣ በግርማ ሞገሱና በውበቱ ስለተማረኩ ከሌሎች ምርኮኛ ፈረሶች ነጥለው ለሰንዓር ንጉሥ ገጸበረከት አቀረቡለት፡፡ በዚህ ጊዜ ንጉሡና የንጉሡ ወታደሮች ዓይኖቻቸውን በዞብል (ሱቤ) ላይ ሰቅለው ውበቱን ማድነቅ ጀመሩ፡፡ በተለይ በሱቤ(በዞብል) ውበት የተደነቀው ንጉሥ በወቅቱ የአገሩ ጦር ድል ለማድረግ የበቃበትን ሁኔታ ማወደስና የድሉን ደስታ ምክንያት በማድረግ ወታደሮቹን ግብር ማስገባት ነበረበት፡፡ሆኖም በፈረሱ ላይ ባደረበት አድናቆት የተነሳ ማድረግ የሚገባዉን ሁሉ ረስቶት ነበር፡፡"

*(ጌታቸው ክብረሥላሴ፣1997፣70)*

**፪. በሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች ዙርያ አንቀጽ መጻፍ የሚያስችሉ አንዳንድ መንደርደሪያ ዓረፍተነገሮችን ጻፉና አንዱን በመምረጥ አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡**

1. በትምህርት ቀናት የአሥራአምስት ደቂቃ የእረፍት ጊዜዬ፤
2. የትምህርት ቤታችን ትንሿ የሬዲዮ መገናኛ ("ሚኒሚዲያ") አገልግሎት፤
3. አካል ጉዳተኝነትና ሥራ፤
4. የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ጠቀሜታ፤
5. የትምህርት ቤታችን የአካባቢ ጥበቃ ክበብ፤

© MoE, FDRE, Not to be reproduced

**፫. የሚከተለውን ጽሑፍ በማንበብ ማስታወሻ ከያዛችሁ በኋላ አሳጥራችሁ አቅርቡ፡፡ (ማስታወሻ አያያዝን በተመለከተ በምዕራፍ አንድ የተማራችሁትን አስታውሱ)**

“በወንጂ ከሸንኮራገዳ እርሻ በሰንሰለት ታስሮ፣ በጋሪ ተጭኖ የመጣው ሸንኮራገዳ ተመዝኖ መጠኑ ከታወቀ በኋላ ሰንሰለቱ ተፈትቶለት ወደ መሸረካከቻ ቦታ ይቀርባል፡፡ አገዳው ከተሸረካከተም በኋላ በመዳመጫው ወፍጮ ጥርስ ይገባል፡፡ ወፍጮው አገዳውን ፈጭቶ ወለላውን ከገለባው ይለየዋል፡፡”

“ወፍጮ ውስጥ ገብቶ የነበረው አረንጓዴ ሸንኮራገዳ ፈሳሽ ወለላ ሆኖ ከወፍጮው በሚወጣበት ጊዜ መልኩን ቀይሮ ቢጫ ይሆናል፡፡”

“ቢጫው ወለላ እንደመረብ በተተበተቡ ቧንቧዎች ውስጥ አልፎ ግዙፍ ወደሆኑ የብረት ጋኖች ተጋብቶ ይቆያል፡፡ ቀጥሎ ያለውን ሥራ የሚያከናውኑ ሌሎች ባለሙያዎች አሉ፡፡ እነዚህም የቅመማ ክፍል ሠራተኞች ወይም ‹ኬሚስቶች› ተብለው ይጠራሉ፡፡ የቀማሚዎች ወይም የ “ኬሚስቶች” ዋነኛ ሥራ ፈሳሹ ወለላ ንፅሕናውን እንዲጠብቅ ማድረግ ነው፡፡”

"… የቅመማ ባለሙያዎች ከወለላው ናሙና እየወሰዱ በቤተ ሙከራቸው ይመረምሩታል፡፡ ፈሳሹም ውስጥ ድኝና ኖራ በመጨመር ከማንኛውም ጉድፍ እንዲጣራ ያደርጉታል፡፡"

"… ቀጥሎ ፈሳሹ ወደ ጠጣርነት መለወጥ ስላለበት ውሃው ፈልቶ በትነት እንዲወጣ ይደረጋል፡፡ ወለላው ወደ ጠጣርነት በሚለወጥበት ክፍል ረጅም ጊዜ ከቆየ ስኳሩ ግርድፍ ይሆናል፡፡ ለአጭር ጊዜ ብቻ ከቆየ ግን ደቃቅ ይሆናል፡፡ የአንኳሩ መጠን እንደ ተፈላጊነቱ ይሆናል ማለት ነው፡፡"

© MoE, FDRE, Ethiopia Not to be republished

"…. ስኳር ግርድፍም ይሁን ደቃቅ መልኩ አንደበረዶ የነጣ ነው፡፡ ስኳሩ ወደንጣት ከመለወጡ በፊት በሶስት ዓይነት የቀለም ለውጥ ደረጃ ያልፋል፡፡ በሸንኮራገዳነት እያለ መልኩ አረንጓዴ፣ አልፎ አልፎ ደግሞ ቡናማ ነው፡፡ ቀጥሎ ሸንኮራገዳው ፋብሪካ ውስጥ ሲገባ ቀለሙ ወደ ቢጫ ወለሳነት ይለወጣል፡፡ በመጨረሻም በፋብሪካው ውስጥ ወደ ስኳርነት ሲለወጥ መልኩ ነጭ ይሆናል፡፡ ቡናማ ስኳር ሲያስፈልግ ቡናማ ቀለም እንዲይዝ ይደረጋል፡፡"

" ከዚህ በኋላ ለገበያ እስኪቀርብ ስኳሩ በመቶና በሃምሳ ኪሎ ጆንያ ውስጥ ገብቶ ወደማከመቻ አዳራሽ ተወስዶ ከዚያ ያቆያል፡፡

*(ሣህለሥላሴ ብርሃነማርያም፤ 1992:75-83)*

**፬. ከሚከተሉት ክበቦች ውስጥ የአንዱን ክበብ የሥራ አፈጻጸም በሚመለከት፣ የተካሄዱ ተግባራትንና ሳይካሄዱ የቀሩ ተግባራትን የሚገልጽ ሐሳብን የያዘ ደብዳቤ የትምህርት ቤታችሁን አድራሻ በመጠቀም ጻፉ፡፡ የጻፋችሁትን ደብዳቤ ለጓደኞቻችሁ አሳዩና በሚሰጧችሁ አስተያየት እንደገና አሻሽሉ፡፡**

1. የሥነጽሑፍ ክበብ
2. የተውኔት ክበብ
3. የ"ኤች. አይ. ቪ. ኤድስ" ክበብ
4. የበጎ አድራጎት ክበብ
5. የሥነዜጋ ክበብ፣ ወዘተ.

## ክፍል ሦስት፡- ንግግር

**፩.ከሚከተሉት ርዕሶች መካከል አንደኛውን በመምረጥ እና አስፈላጊውን መረጃ በማዘጋጀት ተወያዩ፡፡**

ሀ) የውሃ ቀን                    ሐ) የስደተኞች ቀን

ለ) የሴቶች ቀን                  መ) የአዛውንቶች ቀን

**፪. ከመገናኛ አውታሮች ባገኛችኋቸው ወቅታዊ ጉዳዮች(ኤች አይ ቪ፣ ሙስና፣ የጾታ እኩልነት፣ ወዘተ.) ላይ በቡድን ሆናችሁ ተጨዋወቱ፡፡**



© MoE, FDRE Not to be reproduced

፫. መገናኛ ብዙሃን ባይኖሩ በዓለም ላይ ምን ይፈጠር ነበር ትላላችሁ? በቡድን ሆናችሁ ተወያዩና በጋራ ውይይት ድምዳሜ ላይ ድረሱ።

፬. የሸንኮራገዳ ተክል እንዴት እንደሚመረትና በፋብሪካ ውስጥ ወደ ስኳር ምርትነት እንዴት እንደሚለወጥ በማስታወሻችሁ ላይ ተመሥርታችሁ ለጓደኞቻችሁ ገለጻ አድርጉ።

## ክፍል አራት፡- ሰዋስው

፩. ከሚከተሉት ቃላት አምስቱን ምረጡና ስማዊ ሐረጎችን መሥርቱ፤ ከዚያም ዓረፍተነገር ሥሩባቸዉ።

| ምሳሌ፣ • ረጅም ገመድ፣ | • የእግር መንገድ፣ | • የፈተና ወረቀት፣ |
|---|---|---|
| • ረጅም | • መንገድ | • ወረቀት |
| • ትልቅ | • ሰው | • አካፋ |
| • ቀይ | • ቤት | • ብዕር |
| • አዲስ | • ሹራብ | • መጽሐፍ |
| • ሰባራ | • ምጣድ | |

፪. በሚከተሉት ቃላት አምስት ቅጽላዊ ሐረጎችን በመመስረት ዓረፍተነገር ሥሩባቸውና ለጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

| ምሳሌ፣ • የልጅ አዋቂ | • የሕፃን ብልጥ | • የተማሪ ብልህ |
|---|---|---|
| • አዋቂ | • ብልህ | • ደግ |
| • አዋኪ | • የልጅ | • የተማሪ |
| • ብልጥ | • የሕፃን | • ቁም ነገረኛ |
| • የወጣት | | |

© MoE, FDR
Not to be rep

© MoE, FDRE
Not to be reproduced

## ዓረፍተነገር

ዓረፍተነገር ከስማዊ ሐረግና ከግሳዊ ሐረግ ይመሠረታል፡፡ ስማዊ ሐረግ የዓረፍተነገር የባለቤት ክፍልን የሚያመለክት ሲሆን፣ ግሳዊ ሐረግ ደግሞ የዓረፍተነገር የማሰሪያ አንቀጽ ክፍልን ያመለክታል፡፡

**ምሳሌ**፣ ሰዓት አሳልፎ የመጣው ልጅ፣ የመጀመሪያው ክፍለ ጊዜ ትምህርት አመለጠው፡፡

በቀረበው ዓረፍተነገር ውስጥ "ሰዓት አሳልፎ የመጣው ልጅ" ስማዊ ሐረግ ሲሆን፣ የዓረፍተነገሩ የባለቤት ክፍል ነው፡፡

".. የመጀመሪያው ክፍለ ጊዜ ትምህርት አመለጠው" የሚለው ግሳዊ ሐረግ ሲሆን፣ የዓረፍተነገሩ የማሠሪያ አንቀጽ ክፍል ነው፡፡

የዓረፍተነገር ዓይነቶች ሁለት ናቸው፤ ተራ እና ውስብስብ ዓረፍተነገር ይባላሉ። ተራ ዓረፍተነገር ከአንድ ማሠሪያ አንቀጽ ብቻ ሊመሠረት የሚችል ሲሆን ውስብስብ ዓረፍተነገር ደግሞ ከሁለት እና ከሁለት በላይ ማሰሪያ አንቀጾች(ግስ ከሆኑ ቃሎች) ይመሠረታል፡፡

**ምሳሌ**፣ ሀ. አርሴማዊት ብቻዋን አንድ ሊትር ወተት ጠጣች፡፡

በቀረበው ዓረፍተነገር ውስጥ ያለው ማሰሪያ አንቀጽ አንድ ብቻ ("ጠጣች") በመሆኑ ዓረፍተነገሩ ተራ ዓረፍተነገር ይባላል፡፡

ለ. ዘርትሁን የክፍል ጓደኞቿን ሰብስባ ችግሯን አወያየቻቸው፡፡

በ"ለ" በቀረበው ዓረፍተነገር ውስጥ ሁለት ማሰሪያ አንቀጾች ወይም ግሶች (ሰብስባ እና አወያየቻቸው) ስላሉ ውስብስብ ዓረፍተነገር ነው፡፡ ዓረፍተነገር "ለ"ን ለሁለት መክፈል ይቻላል፡፡

ዘርትሁን የክፍል ጓደኞቿን ሰበሰበች፡፡

ዘርትሁን ለክፍል ጓደኞቿ ችግሯን አወያየቻቸው፡፡

**፫. የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች እያንዳንዳቸውን በስማዊ ሐረግና በግሳዊ ሐረግ ከፍላችሁ በሰንጠረዥ በማቅረብ፣ ዓረፍተነገሮቹን በስማዊ ሐረግና በግሳዊ ሐረግ ለመክፈል ምክንያት የሆናችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርባችሁ ተነጋገሩበት።**

***ምሳሌ፣*** *ትናንት የመጣችው ተማሪ በኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተና ከፍተኛ ውጤት አመጣች።*

| ስማዊ ሐረግ | ግሳዊ ሐረግ |
|---|---|
| ትናንት የመጣችው ተማሪ | በኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተና ከፍተኛ ውጤት አመጣች። |

1. ሁለት መሉ ልብስ እንድታሰፋ ጓደኛዋ ገንዘብ ሰጣት።
2. ቁርሳቸውን በልተው በጥዋት ወደ ትምህርት ቤት የመጡት ተማሪዎች የቅርጫት ኳስ ይጫወታሉ።
3. ጓደኞቻችን ጥዋት ጥዋት ተነስተው ስፖርት ስለሚሠሩ ቀልጣፎች ናቸው።
4. ታናሽ እህቴ ከቤተሰባችን ሁሉ የተለየች ባለሙያ ናት።
5. ንጽሕናው ያልተጠበቀ ምግብ የበላው ተማሪ ታመመ።

**፬. ከሚከተሉት ዓርፍተነገሮች ውስጥ ተራ እና ውስብስብ የሆኑትን በመለየት "ተራ" እና "ውስብስብ" ያላችሁባቸውን ምክንያቶች ለይታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።**

1. ልጄ ዛሬ ጥዋት ብዙ ጥያቄዎች አቀረበልኝ።
2. ጨዋታውን ፊት ለፊት በማየቴ ደስ አለኝ።
3. ግርማ ሆስፒታል ሄዶ ወንድሙን ጠየቀ።
4. መኪና እንዳይገጫት ስለፈራች መንገዱን ተሻግራ ሄዳ ዶሮ ለመግዛት አልፈለገችም።
5. እንግዳው ሰውዬ ዛሬ ጥዋት ወደ ሀገሩ ተመለሰ።

© MoE, FDRE Not to be reproduced

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

## ክፍል አምስት፡- ስነጽሑፍ

### የሥነቃል አሰባሰብ

የዘፈንና የኃዘን ግጥሞች ከየት ይሰበሰባሉ? ከተለያዩ ቦታዎች (ሁኔታዎች) ሊሰበሰቡ ይችላሉ፡፡ እንደዚህ ያሉ ግጥሞች ከመጻሕፍት፣ ከጋዜጦች፣ ከመጽሔቶች፣ ወዘተ ይሰበሰባሉ፡፡ እነዚህን በጥናት ውስጥም ማግኘት ይቻላል፡፡

የዘፈንና የኃዘን ግጥሞች ከመስክም ሊሰበሰቡ ይችላሉ፡፡ ከመስክ ይሰበሰባሉ ሲባል ከመንደር፣ ከቀበሌ (ከተለያዩ ሰዎች) ወዘተ ይሰበሰባሉ ማለት ነው፡፡ እንዴት ይሰበሰባሉ? ከሰነዶች የሚሰበሰቡት፣ እያነበቡ ማስታወሻ በመያዝ ይሆናል፡፡ ከመስክ የሚሰበሰቡት ግን በቃለ መጠይቅ ሊሆን ይችላል፡፡ የሚቀርበው ቃለ መጠይቅ ግን ደረቅ እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የሚቀርበው ቃለ መጠይቅ ጥሩ የመግባባት ችሎታ ያለበት ጭውውታዊ ቃለ መጠይቅ ቢሆን ተመራጭ ነው፤ የተፈለገውን መረጃ ለማግኘት ያስችላልና፡፡

*(ፈቃደ አዘዘ፣1991፣117-122 ከቀረበው ላይ ለደረጃው እንዲያመች ሆኖ የተዘጋጀ)*

**፩. በቡድን ሆናችሁ ከተለያዩ የልቦለድ መጻሕፍት፣ ከጋዜጦች፣ ከመጽሔቶች፣ ወዘተ የተለያዩ የዘፈን የኀዘን እና የሥራ ግጥሞች ሰብስቡ፡፡ በዓይነታቸው (የዘፈን፣ የኀዘን፣ የሥራ...)ከፍላችሁ ይዘታቸውን የሚመለከት መግለጫ ከሰጣችሁ በኋላ፣ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡**

## ማጠቃለያ

የመገናኛ ብዙሃን አገልግሎት በጣም ሰፊ ነው፤ የተሻለ አኗኗርን ለመከተል፣ ራስን ከአደጋ ለመጠበቅ፣ ወዘተ. ከመገናኛ ብዙሃን ብዙ መረጃ ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ ከመገናኛ ብዙሃን የሚገኙ መረጃዎች ለኑሮ በጣም አስፈላጊ ናቸው፡፡ ያለ መገናኛ ብዙሃን መኖር ያስቸግራል፡፡ ስለዚህ ስለመገናኛ ብዙሃን በሰፊው ማጥናት ያስፈልጋል፡፡

ቋንቋ በድምጸ-ልሳናት፣ በቃላት፣ በሐረጋት እና በዓረፍተነገሮች ይገለጻል፡፡ ስለዚህ ሀሳብን፣ በንግግር ሆነ በጽሑፍ ለመቀበል እና ሀሳብን በሁለቱም ለሌላው ሰው ለመግለጽ የሐረጋትና የዓረፍተነገሮችን የአወቃቀር ሥርዓት ማጥናት ተገቢ ነው፡፡ ሀሳብ በጽሑፍ ሲገለጽ የራሱ ሥርዓት አለው፡፡ በጽሑፍ የሚገለጽ ሀሳብ አንቀጽን መሳሪያ ያደርጋል፤ አንቀጽ ደግሞ የራሱ የግንባታ ሥርዓት ይኖረዋል፡፡ በተለያዩ አንቀጾች በሚገለጽ አንድ ርዕስ ውስጥ የመሸጋገሪያ ቃሎችን መጠቀም ይገባል፡፡

የዘፈንና የኀዘን ግጥሞች መሰብሰብና ማጥናት የህብረተሰቡን ባህል፣ ወግና ሥርዓት ለማጥናት አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ የማህበረሰብን ባህላዊ ጉዳዮች ለመረዳት እነዚህን የመሰሉ ሥነ ቃሎችን በመሰብሰብ እና መግለጫ በመስጠት መጨዋወትና መወያየት ያስፈልጋል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የመገናኛ ብዙሃንን የተለያዩ አገልግሎቶች መዝግቡና ለጓደኞቻችሁ አሳዩ፡፡
2. በተለያዩ የኀዘን አጋጣሚዎች የተቀነባበሩ የኀዘን ግጥሞች፣ አገልግሎታቸው ምን እንደሆነ ግለጹ፡፡
3. የተለያዩ ክብረ-በዓላትን መዝግቡና የምታስታውሷቸውንና በእነዚህ ክብረበዓላት የሚዘፈኑ ግጥሞች ጻፉ፡፡
4. ዓረፍተነገር በዋናነት ከምንና ከምን ይመሠረታል?
5. ስነቃል የሚባሉት የትኞቹ ናቸው?



© MoE, FDRE Not to be reproduced

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ስምንት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተገነዘባችሁት የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመገንዘባችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(✓)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ ለሙሉ ካልተገነዘባችሁ ደግሞ የ(x) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | √ | ? | x |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የመገናኛ ብዙሃንን አገልግሎት (ጠቀሜታ) እገልጻለሁ፡፡ | | | |
| 2. | የተለያዩ መገናኛ ብዙሃንን መልእክቶች መግለፅ ችያለሁ፡፡ | | | |
| 3. | በመሸጋገርያና አያያዥ ቃላት ተጠቅሜ ሐረጎችንና ዓረፍተነገሮችን መመስረት ችያለሁ፡፡ | | | |
| 4. | ከተለያዩ ምንጮች የሚገኙ መረጃዎች በማስታወሻ እንዴት እንደሚያዙ ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 5. | የአንቀጽ አጻጻፍ ሥርዓትን ጠብቄ፣ ተገቢዎቹን መሸጋገርያና አያያዥ ቃላትን ተጠቅሜ፣ አንቀጽ መጻፍ ችያለሁ፡፡ | | | |
| 6. | ከተለያዩ መገናኛ ብዙሃንና ከአካባቢዬ የአሰባሰብ ሥርዓቱን ጠብቄ የዘፈን፣ የኃዘንና የሥራ ግጥሞችን መሰብሰብ ችያለሁ | | | |
| 7. | ከተለያዩ ጭውውቶች፣ ውይይቶችና ገለጻዎች የሚተላለፉ ቁምነገሮችን በማስታወሻ መያዝ እንዳለብኝ ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 8. | በውይይት ወቅት የውይይትን ሥርዓት መጠበቅ እንደሚገባ ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 9. | የአጻጻፍ ስርአቱን ጠብቄ የሥራ ደብዳቤ መፃፍ እችላለሁ፡፡ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ (?) እና የ(x) ምልክቶች ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ፣ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

© MoE, FDRE Not to be reproduced